# የወንጌል ኃይል
## በእምነት የሚገኝ ፅድቅ (ክፍል 4)

*"እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን።"*

*(ሮሜ 5፡1)*

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 3፡21-4፡25 ባለው ክፍል ፅድቅ እንዴት እንደሚገኝ አብራርቶ የገለፀ ሲሆን፤ በዚህኛው ምእራፍ ላይ ደግሞ ፅድቅ ለአማኝ የሚያመጣውን ትርፍ ያስረዳል። ይኸውም ጽድቅ በኃጢአት ምክንያት ሊመጣ ካለው ቁጣ (ሮሜ 1፡18-3፡20) መትረፊያ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ዘንድ መቅረቢያና ይህም ቅርበታችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖረን አድርጎናል። ሐዋርያው ሰላም የሚለው ስሜትን  ሳይሆን በእግዚአብሔርና በአማኝ መካከል ያለውን እውነተኛ የሆነ ግንኙነትን አስመልክቶ ነው። ይሄ ሁሉ የሆነው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከከፈለው ዋጋ የተነሳ ነው (ኤፌ. 2፡4-5)። አስቀድሞ ጠላት የነበርን አሁን ግን ወዳጅ ሆነናል (ቆላ. 1፡21-22)።

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሲኖረው በመከራውም ጊዜ ሃሴት ማድረግ ይችላል ምክንያቱም እግዚአብሔር በአማኝ ህይወት አንዲሆኑ የሚፈቅዳቸው ነገሮች ሁሉ አማኝ በባህሪና በትእግስት  ክርስቶስን እንዲመስል በማድረግ በተስፋ ይሞላዋል *"በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራችንም ሐሴት እናደርጋለን፤ ምክንያቱም መከራ ትእግስትን፣ እንዲሚያስገኝ እናውቃለን። ትእግስት ፅናትን፣ ፅናት የተፈተነ ባህርይን፣ የተፈተነ ባህርይ ተስፋን፤ ይህም ተስፋ ለእፍረት አይዳርገንም (ሮሜ 5፡3-5)።*

ከዚህም በመቀጠል እግዚአብሔር ፍቅሩን ለእኛ የገለፀበትን መንገድ ሲያስረዳ *"ገና ደካሞች ሳለን፣ ልክ ጊዜው ሲደርስ፣ ክርስቶስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና" (ሮሜ 5፡6)* ይላል። ሰው የሕግ ጫና በላዩ ላይ ተጭኖበት፣ ማንም ለሰው ልጅ የኃጢአት ስርይት የሚሆንን ዋጋ መክፈል በማይችልበትና ሰው ራሱንም ለማፅደቅ ምንም ማድረግ በማይችልበት በድካሙ ጊዜ (ኃጢአተኛ ሆኖ ሳለ) እግዚአብሔር አንድያ ልጁን በመላክ የራሱን ፍቅር በዚህ እንደገለፀ ያስረዳናል።
እኛም ገና ኃጢአተኞች ሳለን በክርስቶስ በኩል ስለ ተገለፀው የእግዚአብሔር ፍቅር ጌታን እያመሰገንን በእምነት ካገኘነው ፅድቅና ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ሰላም የተነሳ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ኃሴት እያደረግን እንድንመላለስ ጌታ በዚህ ማስተዋል ይሙላን።